መስከረም

* የሶሻሊስት አገሮች የዋጋ ሚና ልምድ

* የአፄ ቴዎድሮስ ታሪካዊ ሚና

* የአፍሪካ ኢኮኖሚ የዕድገት ሁኔታና ያስከተለው ፖለቲካዊ አዝማሚያ

ማርክሳዊ ሌኒናዊ የርዕዮተዓለም መጽሔት

ቅጽ ፰ ቁጥር

ሠኔ 1980

34

ቅጽ 8 ቁጥር **34**
ሠኔ 1980

ማርክሳዊ ሌኒናዊ የርዕዮተዓለም መጽሔት

<u>ማ ው ጫ</u>

ገጽ

* የዝግጅት ገጽ 3

* የሶሻሊስት አገሮች የዋጋ ሚና 9
ከልዩ ልዩ ጽሑፎች የተቀነባበረ

*የአፄ ቴዎድሮስ ታሪካዊ ሚና 37
ጠና ደያ (አቀነባባሪ)

*የአፍሪካ ኢኮኖሚ የዕድገት ሁኔታና ያስከተለው
ፖለቲካዊ አዝማሚያ 50
አበበ ወርቁ

በኢሠፓ ማዕከላዊ ኮሚቴ
ርዕዮተዓለም መምሪያ እየተዘጋጀ በየሦስት ወር የሚወጣ
መስከረም 1973 ተመሠረተ

አድራሻ
የፖስታ ሣጥን ቁጥር — 80001
የስልክ ቁጥር — 113000

የአፄ ቴዎድሮስ ታሪካዊ ሚና

ጠና ደዎ (አቀነባባሪ)

የኢትዮጵያ ሕዝብ በአደረጃጀቱ በመንሥትነት ከታወቀበት ጊዜ ጀምሮ የውጭ ወራሪዎችን ጥቃት እየተከላከለ ነፃነቱን አስከብሮ ኖሯል ። በውስጥም የመደብ ትግል በማካሄድ ለተሻለ ማኅበራዊ ሥርዓት ምሥረታና መጠናከር ሲታገል ቆይቷል ። በከፍተኛ መሥዋዕትነት ነፃነቱን ከመጠበቁም ሌላ ለአዲስ የፍትህ ማኅበራዊ ሥርዓት መሠረት ጥሏል ። ለድሉ መገኘት የሕዝቡ ሚና ወሳኝ ቢሆንም ወሳኝነቱን ማረጋገጥ የሚያስችል አመራር የሚሰጡ ግለሰቦች (መሪዎች) መኖር እጅግ አስፈላጊ ነበር ። የትግሉ ሂደት አንዱ ባሕርይም መሪዎችን መፍጠር ነበር ። አፄ ቴዎድሮስ ይህ ዓይነቱ ትግል ካፈራቸው ስመጥር የኢትዮጵያ መሪዎች አንዱ መሆናቸው ይታወቃል ።

ቴዎድሮስ በ1868* የወደቁበትን የመቅደላን ጦርነት ምክንያት በማድረግ የመቅደላ መቶ ሃያኛ ዓመት መታሰቢያ ሲምፖዚየም (ለጥልቅ ግንዛቤ የምርምር ጽሑፎች የቀረቡበትና ውይይት የተካሄደበት) ከሚያዝያ 6—7 ቀን 1980 (እ·ኢ·አ) በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ተቋም አማካይነት ተዘጋጅቶ ነበር ። በዚህ ሲምፖዚየም ላይ የተለያዩ ምሁራን በተለያዩ ርዕሶች የአፄ ቴዎድሮስን ማንነት ፣ ዓላማና ተግባር የሚገልጹ ጥናታዊ ጽሑፎችን አቅርበዋል ። ከጽሑፎቹ መረዳት እንደሚቻለው ቀደም ብለው ስለቴዎድሮስ በጥልቀት ያልተጤኑ ጉዳዮች ተነሥተዋል ፤ እንደሚታወቀው ሀገራችን ኢትዮጵያ እጅግ በጣም ረጅምና ሰፊ ታሪክ ያላት በመሆኗ በታሪክ ሀብታም ናት ። ሆኖም የተሟላ ትክክለኛ ታሪኳ ገና አልተደረሰበትም ። የተጻፈውም ቢሆን በአብዛኛው በውጭ ዜጎች የቀረበ በመሆኑ በመረጃ እጥረትና ጉድለት ወይም በተለያዩ ዓላማዎች ምክንያት መቅረብ በሚገባው መልክ ቀርቧል ለማለት አያስደፍርም ፤ ስለዚህም በጠባቡ የተጻፈውን ለማስፋት ፣ የተጣመመውን ለማቃናት ፣ ያላወቅናቸውን ለማወቅ ፣ አሁን ያለውን ታሪክ በትክክል ለመቅረጽና ለማስተላለፍ በኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ተቋም የተፈጠረው ዓይነት ዝግጅት ሊበረታታ ይገባል።

ይህ አጭር ጽሑፍ ለሲምፖዚየም በቀረቡት ጽሑፎች ላይ በመመሥረት የተቀነባበረ ነው ። የጽሑፉ ዝግጅት ዋና መሠረት ዶ/ር ሪቻርድ ፓንክረስት "ቴዎድሮስ በለውጥ አራማጅነት" በሚል ርዕስ ያቀረቡት ጥናታዊ ጽሑፍ ነው ። በተጨማሪም ዶ/ር ታደሰ ታምራት "ኮሶ ሻጭ እናት — አዲስ ባህላዊ አመጣጥ" ፣ ሪታ ፓንክረስት "የዳግማዊ አፄ ቴዎድሮስ የመቅደላ ቤተ መጽሐፍት" ፣ ግርማ ኪዳኔ "የቴዎድሮስ እሟሟትና የመቅደላው ዘረፋ" ፣ ማሞ ውድነህ

* በተለይ ካልተጠቀሰ የዘመን አቆጣጠር እ·አ· ነው።

"ቴዎድሮስ በግርማቸው ብዕር" በሚሉ ርዕሶች በሲምፖዚየሙ ላይ ያቀረቡአቸው ጽሑፎችም በመረጃነት አገልግለዋል ። እንዲሁም ተዛማጅ ምንጮች በመጠኑ ጥቅም ላይ ውለዋል ።

የአፄ ቴዎድሮስ አነሣሥ

የግለሰቦች ማንነት የሚቀረፀው በተወለዱበትና በሚኖሩበት ማኅበራዊ ግንኙነት ሁኔታ ነው ። ነገር ግን የሁሉም ግለሰብ ማንነት አንድና ተመሳሳይ ሊሆን አይችልም ፤ ከሌሎች ጐልቶና ልቆ የሚታይ ማንነት ያላቸው ብዙ ግለሰቦች መኖራቸው በታሪክ ይታወቃል ። እንዲህ ዓይነቶች ግለሰቦች በሚኖሩበት ማኅበራዊ ግንኙነት ውስጥ ያሉትን ችግሮችና ቅራኔዎች ባሕርይ በመገንዘብ ተገቢ መፍትሔ ለመስጠት የሚያስችሉ ላቅ ያሉና ወደር የለሽ ተግባራትን በማከናወን በሰው ልጅ ታሪክ ሂደት ላይ ማንነታቸውን በጉልህ ያሳውቃሉ ። አፄ ቴዎድሮስ ለዘመናዊት ኢትዮጵያና ለአንድነቷ ባደረጉት ጥረት በኢትዮጵያ የታሪክ ማኅደር ውስጥ ማንነታቸውን በጉልህ ቀርፀው አልፈዋል ። የቴዎድሮስን ታሪካዊ ሚና ለመረዳት የዘመናቸውን ታሪካዊ ሁኔታዎች መመልከቱ ተገቢ ነው ።

ካሣ በኋላ አፄ ቴዎድሮስ በ1818 ተወለዱ ። ቴዎድሮስ የተወለዱበትና ያደጉበት ሁኔታ በውስጥ ኢትዮጵያ በመሳፍንትና በአካባቢ ባላባቶች የሥልጣን ፉክክር ተወጥራ የግዛት አንድነቷ የመላላት አደጋ ባንዣበበበት ፡ አንድ ወጥ የሆነ ጠንካራ አመራር መስጠት የሚችል ማዕከላዊ መንግሥት በተዳከመበት ወቅት ነበር ። በዓለም አቀፍ አንፃር ሲታይ ደግሞ ካፒታሊዝም አድጎ ከራሱ ብሔራዊ ክልል ውጭ ዛሬ ታዳጊ በመባል የሚታወቁትን አያሌ አገሮችን በቅኝ ግዛትነት ለመያዝ ከፍተኛ ትግል ማድረግ የጀመረበት ነበር ።

በዚያን ዘመን የኢትዮጵያ የውስጥ ዋነኛ ቅራኔ ለአሮጌው የመሳፍንት የአካባቢ አገዛዝ በቆሙ ኃይሎችና አንድ ጠንካራና አዲስ ማዕከላዊ መንግሥት እንዲመሠረት በሚፈልጉ ኃይላት መካከል የሚካሄደው ትግል ነበር ። በውስጥ ሰፍኖ የነበረው የመሳፍንት አገዛዝ አገሪቷን ከማዳከሙ ሌላ ለውጭ ተስፋፊ ኃይሎችና ቅኝ ገዥዎች ምቹ ሁኔታዎችን አመቻችቷል። በጊዜው ኢትዮጵያ ከውጭ የነበረባት ዋነኛ ቅራኔ ደግሞ አንድነቷንና ነፃነቷን በሚፈታተኑ ወራሪ መንግሥታት የተፈጠረ ሲሆን በአንድ በኩል በውጭ ተስፋፊ ኃይሎች በሌላ በኩል ለነፃነታቸውና ለአንድነታቸው በሚታገሉ ኢትዮጵያውያን መካከል መራራ ትግል ተካሂዷል ። በአጭሩ ዋናው ቅራኔ አገሪቷን ያዳከሙ የውስጥና የውጭ ኃይሎችና የአገሪቷን አንድነት መልሶ ለመፍጠርና ለማጠናከር የውስጥና የውጭ ጠላቶቿን ማንበርከክ የሚችል ኃይል ለመፍጠር ወይም ለማደራጀት በሚፈልጉ ኃይሎች መካከል የሚካሄደው ትግል ነበር ። ይህ የታሪክ ወቅት የራሱን ጀግና መፍጠሩ ግዴታ ነበር ። በወቅቱ የተራማጅ አስተሳሰብ የነበራቸው የአፄ ቴዎድሮስ ሚና የተከሰተው በዚህ ሁኔታ ውስጥ ነው ።

አፄ ቴዎድሮስ በጊዜያቸው የነበሩትን ቅራኔዎችና ችግሮች ለመፍታት የሚያስችላቸው የመጀመሪያው ቁልፍ ተግባር አንድ ጠንካራ ማዕከላዊ መንግሥት ማደራጀት መሆኑን ተረዱ ። ያለ ጠንካራ ማዕከላዊ መንግሥት ከውጭ የሚሰነዘረውን የተስፋፊና የቅኝ ገዥዎችን ጥቃት መመከት ፡ ለዘመናት የኖረውን የሥልጣን ሽኩቻና ፉክክር ማስወገድ ፡ ሕዝቡን ማስ

ተባበር ፡ አንድ ማድረግና ማጠናከር እንደማይቻል ተገነዘቡ ። በመሆኑም ተቀዳሚ ዓላማቸው የተጠናከረ ማዕከላዊ መንግሥት ማደራጀት ፣ በእርሱም መሣሪያነት የውጭ ወረራን መከላከልና በውስጥም የሚደረጉትን የተቀናቃኞቻቸውን እንቅስቃሴ መግታት ነበር ። ይህን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ከብዙዎቹ የአካባቢ መሳፍንት ጋር ጦርነት ገጥመው ድል ካደረጉ በኋላ በ1855 ንጉሠ ነገሥት ተብለው ዘውድ ጫኑ ። በኋላም የተቀሩትን ተቀናቃኞቻቸውን ለማንበርከክ ካካሄዱት ከፍተኛ ትግል ጐን ከተስፋፊዎችና ከቅኝ ገዥዎች የሚሰነዘርባቸውን ተንኮል ሁሉ ለመቋቋም ሠራዊታቸውንና ሕዝባቸውን ለማጠናከር ተነሣሡ።

ቴዎድሮስ ውጥናቸውን እውን ለማድረግ አያሌ ተግባራትን አከናውናዋል ። ከእነዚህም መካከል ሲምፖዚየሙ ላይ በቀረቡት ማስረጃዎች እንደተገለጸው 1/ መድፍ ማምረት ፣ 2/ ዘመናዊ ሠራዊት መገንባት ፣ 3/ ሰላምን ማስፈን ፣ 4/ የመንገድ ሥራ ማስፋፋት ፣ 5/ የጀልባ ሥራ ማካሄድ ፣ 6/ የባሪያ ንግድን ማገድ ፣ 7/ የመሬት ይዞታ ለውጥ ማድረግና 8/ የትምህርት ማዕከል የሚሆን ቤተመጻሕፍት ማቋቋም ይገኙበታል ።

1· መድፍ ማምረት ፣

አፄ ቴዎድሮስ በሕጋዊ ወራሽነት ሳይሆን በትግላቸውና በችሎታው የአገር መሪነትን ቦታ ያዙ ። ነገር ግን ሥልጣን መያዝ ብቻውን በቂ አይደለም ። የተቀዳጁትን ሥልጣን ማጠናከርና በአስተማማኝ ሁኔታ ማቆየት ያስፈልጋል ። በዚህ አንፃር ለማዕከላዊ መንግሥት መጠናከር እንቅፋት የሆኑ መሳፍንትንና ባላባቶችን ማስገበር እንዲሁም በአገሪቷ ሰሜን ምዕራብ በኩል የነበረውን የግብጽ የመስፋፋት እንቅስቃሴ መግታት የወቅቱ ወሳኝ ፖለቲካዊ ተግባር ሆነ። ለዚህም ዘመናዊ የጦር ኃይል መፍጠር እጅግ አስፈላጊና ቅድመ ሁኔታ ሆኖ ቀረበ። ሪቻርድ ፓንክረስት እንዳሉት ቴዎድሮስ "... የዓላማቸውን ንድፍ ከግብ ለማድረስ ከፈለጉ ኋላቀር የነበረውን የአገራቸውን የጦርነት ስልት ዘመናዊ በሆነ ስልት መለወጥ እንዳለባቸው በሰሜኑ የአገሪቷ ድንበር በኩል የግብፅ ወታደሮች ከሚያደርጉት እንቅስቃሴ ልምድ ተረድተዋል።" ለዚህም ለውጥ አንዱ አስፈላጊ ነገር ዘመናዊ የጦር መሣሪያ ማግኘት በመሆኑ የአውሮፓ መንግሥታት በተለይም የእንግሊዝ መንግሥት በጉዳዩ እንዲተባበራቸው ጥያቄ አቀረቡ ። ለዘመናዊ መሣሪያና ጥበብ ያላቸውን ፍላጐት በመግለፅ ለአውሮፓውያን ነገሥታት በተደጋጋሚ ደብዳቤዎች ጻፉ ። መልዕክተኞችም ላኩ ። ነገር ግን ለጥያቄቻቸው ከአውሮፓውያን በኩል አርኪ ምላሽ አላገኙም ነበር ። በተጨማሪም ፣ አውሮፓውያን እንደመድፍ የመሳሰሉ ከባድ መሣሪያዎችን ለአፄ ቴዎድሮስ ቢሰጧቸው እንኳን በውስጥና በአካባቢ ኃይላት በነበሩ ጠላቶቻቸው ምክንያት በሰሜን ምዕራብ ኢትዮጵያ መድፍ ማስገባት አስቸጋሪ ነበር ። ይህን ችግር የተረዱት አፄ ቴዎድሮስ በሀገር ውስጥ መድፍ ለመሥራት አቀዱ ። ሪቻርድ ፓንክረስት እንዳቀረቡት ለዕቅዳቸው ተግባራዊነት ሁኔታዎች የተመቻቹላቸው "በ1861 ጃኩዌን የተባለው ፈረንሳዊው ብረት ቀጥቃጭ ጋፋት ይኖሩ የነበሩ እደጥበበኛ አውሮፓውያን ሚሲዮኖች ካገዙት አዳፍኔ መሥራት የሚችል ለመሆኑ ፈቃደኝነቱን ከገለጸላቸው በኋላ ነበር ።" ከዚያም ቴዎድሮስ ሚሲዮናውያኑ ከጃኩዌን ጋር እንዲተባበሩ ጠየቁ ። በዚሁ የመድፉ ሥራ ተጀመረና የብረት ማቅለጫ ምድጃና ወናፍ ተሠራ። ይሁን እንጂ ከደካማ ቁሳቁሶች

የተሠራው የብረት ማቅለጫ የሚፈለገው ብረት ከመቅለጡ በፊት ራሱ በመቅለጡ ሥራው ሊካሄድ አልቻለም ። ጃኩዌንም ዕቅዱ እንዳልተሳካለት ሲያውቅ ንጉሡን ፍቃድ በመጠየቅ ወደ ሀገሩ ተመለሰ ።

ቴዎድሮስ ግን ተስፋ አልቆረጡም ። ሚሲዮናውያን ወደ ነበሩበት ጋፋት በመሄድ ጃኩዌን ያቋረጠውን ሥራ እንዲቀጥሉ ጠየቋቸው ። ሚሲዮናውያኑ ግን የሥራው ልምድም ሆነ ዕውቀት የሌላቸው መሆኑን ለቴዎድሮስ ገለጹላቸው ። ሆኖም የንጉሡን ቅሬታ ለማስወገድ በማሰብ ዋልድማይር የሚባል ሚሲዮናዊ ለጠመንጃ መሣሪያ ሊያገለግሉ የሚችሉ አንዳንድ ክፍሎችን ሠራ ። በዚህ ውጤት የተደሰቱት ቴዎድሮስ የብረት ማቅለጫውን እንዲሠሩ ሚስዮናውያኑን በድጋሚ ጠየቁአቸው ። ሁኔታው በዚህ እንዳለ ሄር ሞሪትዝ የተባለው ሚሲዮናዊ ትናንሽ አዳፍኔዎችንና ጥቂት ጥይቶችን ሠራ ። አፄ ቴዎድሮስ በተገኘው ውጤት የተደሰቱ ቢሆንም የተሻለ ለማምረት የሚያስችል ሥራ አስጀመሩ። ሥራውም ከምን ደረጃ እንደደረሰ ለማወቅና ሠራተኞቹንም ለማበረታታት በተደጋጋሚ ደብዳቤ ይጽፉ ነበር ። በመጨረሻም ጥረቱ በመቀጠሉ በጋፋት የነበሩት አውሮፓውያን አዳፍኔ ለመሥራት ቻሉ ።

ቴዎድሮስ በነበሩባቸው የውስጥ ችግሮችና ከውጭ በሚሰነዘርባቸው የወረራ ሙከራ ምክንያት በሀገር ውስጥ የሚመረተውን መሣሪያ ብቻ መጠባበቅ አልቻሉም ። በጥቅምት 1862 ከእንግሊዝ የጦር መሣሪያ ለመግዛት እንደሚፈልጉ በመግለጽ ለእንግሊዝ መንግሥት በቆንሲል ካሜሩን አማካይነት ጥያቄ አቀረቡ ። ይፈልጓቸው ከነበሩት የመሣሪያ ዓይነቶች መካከልም አዳፍኔ፣ ሮኬቶች ፣ ትናንሽ መድፎች ፣ የእጅ ቦምቦች ፣ ጥይቶች ይገኙባቸው ነበር ።

የእንግሊዝ ውጭ ጉዳይ ቢሮ ቴዎድሮስ በካሜሩን አማካይነት ላቀረቡት ጥያቄ መልስ መስጠት አልፈለገም ። ቴዎድሮስ የመሣሪያ ግዥ ጥያቄያቸውን በመተው መሣሪያ መሥራት የሚችሉ ሠራተኞችን በተጨማሪ ለማስመጣት ጥረታቸውን በመቀጠል ከሚሲዮናውያኑ የእጅ ባለሙያዎች መካከል ማርቲን ፍላድ የተባለውን ሰው ጠመንጃ ሠሪዎችንና ሌሎች የእደ ጥበብ ሙያተኞችን እንዲያመጣላቸው በ1864 ወደ እንግሊዝ ላኩ ። ነገር ግን ለዚሁም ጥያቄያቸው በጎ ምላሽ አላገኙም ። ቴዎድሮስ ተስፋ ባለመቁረጥ ዓላማቸውን ለማሳካት ሆርሙዝ ራሳም በተባለው የእንግሊዝ መልዕክተኛ አማካይነት መድፎችንና ነፍጦችን መሥራት ፣ ብረታ ብረት ማቅለጥ ፣ የከባድ መሣሪያ አጠቃቀምን ማስተማር የሚችሉ ባለሙያዎች ለሥራ ከሚያስፈልጓቸው መሣሪያዎች ጋር እንዲልኩላቸው ለእንግሊዝ መንግሥት መሪዎች ጥያቄ አቀረቡ ። የእንግሊዝ መንግሥት ግን ለዚህ ተደጋጋሚ ጥያቄ መልስ መስጠት አልፈለገም ነበር ።

በዚህ ሁኔታ የተናደዱት አፄ ቴዎድሮስ በሀገር ውስጥ የሚሠራውን መሣሪያ በዓይነትም ሆነ በቁጥር ለማሳደግ በማሰብ አውሮፓውያኑ "1000 ፓውንድ ክብደት ያለው የመድፍ እርሳስ የሚተኮስበት አዳፍኔ እንዲሰሩ" አዘዙ ። ለዚህ ሥራ የሚውሉ ሀብቶች ለምሳሌ እንደ ነሐስ ያሉትንና ሌሎችንም ከተለያዩ የሀገሪቷ ክፍሎች እንዲሰባሰቡ አደረጉ። በኋላም ከዚህ በፊት በኢትዮጵያ ታይቶ የማይታወቅና ክብደቱ ሰባት ቶን የሚሆን ትልቅ መድፍ ለመሥራት ተቻለ ።

ቴዎድሮስ በዚህ ሁኔታ የተወሰነ የመሣሪያ ክምችት ለማግኘት ችለው ነበር ። ሪቻርድ ፓንክረስት እንዳሉት ንጉሡ 24 የነሐስ መድፎች ፣ በኢትዮጵያ የተሠሩ አራት መድፎችና ዘጠኝ የነሐስ አዳፍኔዎች ነበሯቸው ።

በሪቻርድ ፓንክረስት አስተያየት የቴዎድሮስ የጦር መሣሪያ ሥራ ፍሬ ማሳየት "በተወሰነ መልኩ የኢትዮጵያ እንዱስትሪ አብዮት" ነበር ማለት ይቻላል ፤ ነገር ግን ከቴዎድሮስ ሞት ጋር እንዲህ ዓይነቱ የዘመናዊ ቴክኖሎጂ ባለቤት የመሆንና መሣሪያ የማምረት ጥረት አከተመ ። የተመረቱትም ቢሆኑ በመቅደላው ጦርነት ወደሙ ።

2· የዘመናዊ ሠራዊት ግንባታ

ቴዎድሮስ በጊዜያቸው ለነበሩት ችግሮችና ቅራኔዎች መፍትሔ በማስገኘት አንድነቷ የጠበቀ አገር ለመፍጠርና ሥልጣኔ ለማስፋፋት የሚችሉት ዘመናዊ የጦር መሣሪያ በማስገባትና በማሠራት ብቻ እንዳልሆነ ተገንዝበዋል ። ዘመናዊውን መሣሪያ መታጠቅ ፤ መጠቀምና ለተፈለገው ዓላማ ማዋል የሚችል ሠራዊት በአዲስ መልክ ማደራጀትም ዓላማቸው ነበር ። ሪቻርድ ፓንክረስት እንደገለጹት ቴዎድሮስ በዲሲፕሊን ባልታነጸና በሥርዓት ባልተደራጀ ጦር ምትክ የሠለጠነ ፡ በዲሲፕሊን የሚመራና ደመወዝ የሚከፈለው ዘመናዊ ሠራዊት ለማቋቋም ከፍተኛ ፍላጐት ነበራቸው ።

ቴዎድሮስ ይህን ዓላማቸውን እውን የማድረግ እርምጃ መውሰድ የጀመሩት ገና ንጉሥ ከመሆናቸው በፊት መሆኑን ሪቻርድ ፓንክረስት ባቀረቡት ጽሑፍ ገልጸዋል። ቴዎድሮስ ከመንገሣቸው ሁለት ዓመታት አስቀድመው (1853) በዲሲፕሊን የታነፀ ሠራዊት ነበራቸው ። ለወታደሮቻቸው በየጊዜው የተወሰነ ደመወዝ መክፈልም ጀምረው ነበር ።

ቴዎድሮስ ለሠራዊታቸው ቋሚ ደመወዝ ለመመሥረት ሕግ ማውጣትና መወሰን ብቻ በቂ አለመሆኑን በመገንዘብ ሠራዊታቸውን በትምህርት ለማጐልበት ጥረት አድርገዋል ። ወታደሮቻቸው ቀደም ሲል እንደነበረው የገበሬ ጐተራ መገልበጥ ፡ ከብቶች ማረድ ፡ ልብስ ፡ ንብረትና ገንዘብ መዝረፍ እንደሌለባቸውና በሚሰጣቸው ቋሚ ደመወዝ የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ መግዛት የሚችሉ መሆናቸውን አስተምረዋል ። ነገር ግን ይህ ውጥናቸው በሀገሪቱ ውስጥ ባጋጠሟቸው ፖለቲካዊና ወታደራዊ ችግሮች ምክንያት በፈለጉት መጠንና ዓይነት ተግባራዊ አልሆነም።

3· ሰላምን ማስፈን

የዘመነ መሳፍንት የእርስ በርስ ጦርነት ማዕከላዊ የመንግሥት ሥልጣንን በማዳከሙ ለሽፍቶች መበራከትና ለዘረፋ መስፋፋት መንሥኤ ሆኗል ። የቴዎድሮስ አንዱ ዓላማ ይህን ሁኔታ ማስተካከልና ሰላምን ማስፈን ነበር ። የዚህ ዓይነቱን የዕድገት እንቅፋት ለመግታት አፄ ቴዎድሮስ በ1855 ወዲያውኑ እንደ ነገሡ እያንዳንዱ ሰው ሕጋዊ ወደ ሆነው ሙያው ማለትም ነጋዴው ወደ ንግዱ ፤ ገበሬው ወደ እርሻው መመለስ እንዳለበት የሚያስገነዝብ አዋጅ አወጡ ። በፓንክረስት አስተያየት አዋጁ በእርስ በርስ ጦርነት ታውካ በነበረችው ሀገር ውስጥ ሰላምና ብልጽግናን ለማስፈን ዓይነተኛ መሣሪያ ነበር ፤ በአዋጁ መሠረት የንግድ መተላለፊያ በሆኑ መንገዶችና በሌሎችም ሥፍራዎች ከዘረፋና ከውንብድና ሥራቸው ያልተቆጠቡ ግለሰቦችን ለመቆጣጠር ተችሏል ። ውጤትም በመግኘቱ ከዚያ በፊት በወንበዴዎች ተግባር በእርስ በርስ ጦርነት ሰላምና ፀጥታ በመጥፋቱ ተዘግተው የነበሩት የንግድ መንገዶች ሊከፈት በቅተዋል ።

4· የመንገድ ሥራ ፤

ቴዎድሮስ ለዓላማቸው መሳካት ይታገሉ የነበረው ከሰው ጋር ብቻ ሳይሆን ከተፈጥሮም ጋር ነበር ። የሀገሪቷ ወንዞች ፤

ተራሮች ፡ ቆላማና በረሃማ አካባቢዎች ሠራዊታቸውንና መጓሪያዎቻቸውን እንደ ልብ አንቀሳቅሰው ጠላቶቻቸውን ማንበር ከክ አላስቻሉአቸውም ። ለዚህ አንዱና ዋንኛ መፍትሔ ሆኖ ለቴዎድሮስ የታያ ቸው ሠፋፊ መንገዶች መሥራት ነበር ። ነገር ግን ዘመናዊ መንገድ ለመሥራት የሚያስችል የሠለጠነ የሰው ኃይልና መሣ ሪያ አልነበራቸውም ። ይህ ችግር ቢኖርም ሕዝቡን በማስተባበርና ጥቂት አውሮፓው ያንን (ሚስዮናውያን በማሰማራት ለመጀመ ሪያ ጊዜ በኢትዮጵያ ውስጥ ደብረታቦርን – ከጐንደር ፡ ከጐጃምና ከመቅደላ ጋር የሚያ ገናኝ መንገድ ሥራ ተጀመረ ። ቴዎድሮስ ሕዝቡ የመንገዱን ሥራ በርትቶ እንዲያካ ሂድ እራሳቸው አርአያ በመሆን ተሰልፈ ዋል ። ሪቻርድ ፓንክረስት እንዳሉት ቴዎ ድሮስ የመንገድ ሥራ ዓላማቸውን ለማሳ ካት የሞከሩት በሥራው በመሳተፍ ነበር። በተለይ ከእንግሊዝ ጋር የነበራቸው ግንኙ ነት እየተበላሸና ወደ ጦርነት እያመራ በሄደበት ወቅት መድፋቸውን ከደብረታ ቦር ወደ መቅደላ የጦር ምሽግ ለመውሰድ በነበራቸው ጉጉት ምክንያት በመንገድ ሥራው ላይ ያሳዩት ትኩረት ከፍተኛ ነበር። "ከማለዳ ጀምረው እስከሌሊቱ ድረስ ይሠሩ ነበር ። በእጆቻቸው ድንጋይ በማገላበጥ ፡ መሬት በመደልደል ፡ ወይም ጉድጓዶችን በመሙላት ይረዳሉ ።" ይህ ጥረታቸው በሕዝባቸው ላይ ያሳደረው የሥራ ግፊት ቀላል አልነበረም ።

የመንገድ ሥራው ግን እንደተፈለገው የሚፋጠን አልነበረም ። ሥራው በሳይንስና ቴክኖሎጂ ውጤቶች ያልታገዘ በመሆኑ ብዙ ጊዜና ጉልበት የሚፈጅ ነበር ። ይህም ሆኖ ግን ንጉሡ ከሥራው ወደ ኋላ አላ ሉም። ብዙም ባይገፉላቸው የተሠራው መንገድ ጥራት ተደንቋል ። ለምሳሌ የእንግ ሊዝ ወታደራዊ የዘመቻ ኃይል አባል የነበ ረው ካፒቴን ሆዜየር ወደ መቅደላ የሚወስ ደውን የቴዎድሮስን መንገድ ሲያደንቅ "የጥንታዊ ምሕንድስና ታላቅ ጥበብ ነው። በብዙ ጉልበትና ጊዜ አለቶች እየተነቃቀሉ ወደ ጐን ተደርገዋል። ወይም እየተቀደዱ መተላለፊያ በውስጣቸው ተሠርቷል ።" በማለት ዘግቧል። የጂኦግራፊ ሰው የነበ ረው ማርክሃምም ስለዚሁ መንገድ ሥራ ሲመሰክር "እጅግ አስደናቂ ሥራ ነው ፤ የማይሞትና የማይሞከር ጠንካራ ሐውልት ነው" ብሏል ። ከአውሮፓውያን ሚሲዮና ውያን አንዱ የነበረው ፍላድም አጼ ቴዎድ ሮስ በመንገድ ሥራው ላይ ያሳዩትን ልዩ ጥንካሬ በአድናቆት ሲገልጽ "በእርግጥ እርሳቸው (አፄ ቴዎድሮስ ማለቱ ነው) የማይበገሩ ብረት ናቸው" በማለት ጽፏል። አፄ ቴዎድሮስ በተሠሩት መንገዶች ላይ ለመጓጓዣ የሚሆን ባለተሽከርካሪ ጋሪ አሠ ርተው በሥራ ላይ አውለው ነበር ።

5· የጀልባ ሥራ

አፄ ቴዎድሮስ ጀልባ በማሠራት በጣና ሐይቅ ላይ የጉዞ መሥመር ለመዘርጋት አስበው ነበር ። ቴዎድሮስ ይህን ሲያስቡ ሪቻርድ ፓንክረስት እንደገለጹት "አነስ ተኛ የባሕር ኃይል እንዲኖራቸው የፈለጉ መሆናቸው ጥርጥር የለውም ። ቴዎድሮስ አውሮፓውያን የእጅ ባለሙያዎች ጀልባ እንዲሠሩላቸው ጠየቁአቸው ። እነርሱም ጀልባ ለመሥራት የሚያስችል ሙያ የሌላ ቸው መሆኑን ገለፁላቸው ። ከዚህ በኋላ ቴዎድሮስ ራሳቸው የጀልባውን ሥራ ጀመሩ ። ከብርቱ ጥረት በኋላም ከታቹ ጠፍጣፋ የሆነ ትልቅና ወፍራም ፣ ለማሽከ ርከር የሚያስችሉ በእጅ የሚንቀሳቀሱ ሁለት ሰፋፊ መቅዘፊያዎች ያሉት ጀልባ ሠሩ ።" ጀልባው በነዳጅ የሚንቀሳቀሰውን ዓይነት ቀዛፊ ጀልባ ሲሆን የጐደለው ክፍል ሞተር ብቻ መሆኑን በወቅቱ የዐይን

ተመልካቹ የመሠከሩ መሆኑን ሪቻርድ ፓን
ክረስት ባቀረቡት ጽሑፍ ገልጸዋል።

የጀልባ ሥራው ቀጥሎ ርዝመታቸው 60፣ ስፋታቸው 20 ጫማ የሆነ ከእንጨት የተሠራ ወለል የነበራቸው ፤ በእጀታ ሊዞሩና እያንዳንዳቸው መቶ ሰው መያዝ የሚችሉ የሁለት ሰፋፊ ጀልባዎች ሥራ ተጠናቀቀ ። ይሁን እንጂ አጼ ቴዎድሮስ ተቀናቃኞቻቸው በውስጥና በውጭ በፈጠሩባቸው ፖለቲካዊ ችግርና ግፊት በመውደቃቸው የጀልባው ሥራ ሊቀጥልና ሊስፋፋ አልቻለም ።

፮· የባሪያን ንግድ ማገድ

ከ16ኛው ምዕት ዓመት ጀምሮ ለሦስት ተከታታይ ምዕት ዓመታት በቆየው የባሪያ ንግድ በባርነት ተሽጠው ወደ አሜሪካ የተጋዙት አፍሪካውያን ወደ 100 ሚሊዮን ይጠጋሉ ፤ ከእነዚህም ውስጥ ኢትዮጵያውንም ነበሩ። ይህ የባሪያ ንግድ የሌሎችን የአፍሪካ ሀገሮች የምርት ኃይል እንደገታ ሁሉ የኢትዮጵያንም ዕድገት ካቀጨጩ ዋና ዋና ምክንያቶች አንዱ እንደነበር ይታወቃል ። አውሮፓውያን ባሮችን የፈለጉት ለጉልበታቸው ነው ። ብዙ መሥራትና ማምረት የሚችሉት ደግሞ በወጣትነት ዕድሜ ክልል ውስጥ ያሉ ጠንካራና ጤናማ የሆኑ ብቻ ናቸው ። ይህን አምራች የኅብረተሰብ ክፍል ማጣት ማለት የምርት ኃይል ዕድገት መገታት ማለት ነው ። ከዚህም በተጨማሪ ባሮችን ማግኘት የሚቻለው በአመዛኙ በጦርነት ነበር ። በመሆኑም ለባሪያ ፍንገላ ሲባል የተካሄዱ ጦርነቶች በፊውዳላዊ ፉክክር ምክንያት በተለያዩ ጐሣዎች ፤ ብሔረሰቦችና አካባቢዎች በሚኖሩ ሕዝቦች መካከል ያለማቋረጥ ከተካሄዱ ጦርነቶች ጋር በመዳመር በኢትዮጵያ ለምርት ኃይል ዕድገት መቀጨጭ አንድ ምክንያት ሆነዋል ። የአፄ ቴዎድሮስ አንዱ ዓላማ ይህን አስከፊ ሁኔታ ማቆም ነበር ።

የባሪያ ንግድን በሚመለከት ቴዎድሮስ የነበራቸውን አቋም ሪቻርድ ፓንክረስት ሲገልጹ "ቴዎድሮስ ሕይወታቸውን ሙሉ የባሪያ ንግድ ጠንካራ ተቃዋሚ ነበሩ" ብለዋል ። ንጉሠ ነገሥት ተብለው ከመንገሣቸውም በፊት ይህን ጠንካራ አቋማቸውን በሚገባ አሳይተዋል ፤ ከነገሡ በኋላም አቋማቸውን ተፈጻሚ ለማድረግ አዋጅ አውጥተው ተግባራዊ እንዲሆን ጥረት አድርገዋል ። ነገር ግን የባሪያን ንግድ ወዲያው ለማቆም ቀላል ተግባር ሆኖ አልተገኘም ። በዚህም ምክንያት ቴዎድሮስ አዋጃቸውን ከረር አድርገው "ባሪያ ሲሸጥ የተገኘ ማንኛውም ሰው ቀኝ እጁንና ግራ እግሩን ይቆረጣል ።" በማለት አዘዙ ። ይህም ሆኖ ግን በነበራቸው የውስጥ የፖለቲካ አለመረጋጋትና የውጭ ኃይል ተፅዕኖ ምክንያት የባሪያ ንግድን የማስቀረት ዓላማቸውን ከግብ አላደረሱትም ።

፯· የመሬት ይዞታ ለውጥ

ቴዎድሮስ ሲነግሡ የመሬት ይዞታ ሕግና ሥርዓት ያልነበረ በመሆኑ ልዩ ልዩ ችግሮች መንሥዔ ነበር ። ሪቻርድ ፓንክረስት እንደገለጹት ቴዎድሮስ ችግሩን ለማስወገድ በሕግና ሥርዓት የታወቀ የመሬት ይዞታ ሥሪት ለመመሥረት ጥረዋል ። "ሸዋን በቁጥጥራቸው ሥር ካደረጉ በኋላም የአፋሽነትን መብት በማጠናከር የመሬት ይዞታ ሥርዓቱን ለመለወጥ ሞከሩ ። በዚሁ መሠረት ቴዎድሮስ በሸዋ ውስጥ የመሬት የግል ይዞታን የሚያቋቁም አዋጅ አውጥተዋል ። በአዋጁ መሠረት እያንዳንዱ ሰው ቀደም ሲል አባቶቹ በይዞታነት ያቆዩትን መያዝ ይችላል ፤ የዚህ ዓይነቱ አጋጣሚ የሌላቸው ሰዎች ካሉ ደግሞ ንጉሡን እንደ አባት በማየት መሬት መያዝ (ማግኘት) ይችላሉ ።"

አፄ ቴዎድሮስ በሸዋ ብቻ ሳይሆን በሰሜን በተለይ በአካለ ጉዛይና በሰራዬ ተመሳሳይ የምሬት ይዞታ ለውጦችን አድርገዋል ። ነገር ግን አዋጁ ከወጣ በኋላ በተለይ በሸዋ ውስጥ በመሬት ይዞታ ላይ ጭቅጭቅ ተነሣ። በተለይ ለአፄ ቴዎድሮስ አስቸጋሪ የሆነባቸው የቤተክርስቲያን የመሬት ይዞታ ነበር ። የኦርቶዶክስ ክርስትና መሪ ዎች በሃይማኖት ስም በሰፋት የያዙትን መሬት ለአራሹ ለመልቀቅ አልፈለጉም። ሪቻርድ ፓንክረስት እንደገለጹት ቴዎድ ሮስ ስለዚህ ይዞታ ተቃውሟቸውን ሲገልጹ "እናንተ የመስቀል መሬት ነው ብላችሁ ሁሉንም መሬት ወስዳችሁ ፤ እኔስ ምን ልብላ ፤ ለወታደሮቼስ ምን ልስጥ ።" በማለት ተናግረዋል ።

ይሁን እንጂ የቤተክርስቲያንና የሃይማ ኖት መሪዎችን የመሬት ይዞታ የማከፋፈል ዕቅዳቸውን እስከ 1860 አቆይተውታል ። በ1860 ግን ለገበሬዎች እንዲከፋፈል አድር ገዋል ። አፄ ቴዎድሮስ ይህን ዓይነት እርምጃ ሲወስዱ ቤተክርስቲያን ወይም ሃይማኖትን ለማጥቃት ፈልገው አልነበ ረም ። ሪቻርድ ፓንክረስት እንደጠቀሱት ለራሳቸው በጣም ቀላልና እጅግ ያልተመ ቻቹ ሁኔታ ውስጥ እየኖሩ ፤ ወታደሮቻቸ ውን ማኖርና ለሀገሪቷ መሻሻል የሚጠ ቅሙ እርምጃዎችን መውሰድ የሚያስችል ገቢ ለማግኘት ነበር ። ቴዎድሮስ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚሠሩ ቄሶችም ቁጥር ከ፭ እስከ 7 ብቻ እንዲሆን በመወሰን ሌሎቹ በምርት ሥራ ላይ እንዲሠማሩ አዘዙ ።

ቴዎድሮስ ለሀገር አንድነትና ነፃነት መጠበቅና ለሕዝብ ኑሮ መሻሻል ይበጃል ብለው የወሰዷቸው እርምጃዎች በጥቂት የሃይማኖት መሪዎችና ደብተራዎች የማይ በጁ መስለው በመታየታቸው ምክንያት የተሰነዘረባቸው ተቃውሞ ከፍተኛ ነበር ። ይህም ዓላማቸው ዳር እንዳይደርስ እንቅ ፋት ከፈጠሩባቸው ሁኔታዎች አንዱ ነበር።

፰.ቤተመጻሕፍት ማቋቋም

ቴዎድሮስ ብዙ የማይታወሱበት ነገር ግን እጅግ ጠቃሚ የሆነ ሌላ ዓላማም ነበራቸው ። ይኸውም ትልቅ ቤተመጻሕ ፍት ለመመሥረት የወጠኑት ሐሳብ ነው ። የቤተመጻሕፍቱ ሥራ ቴዎድሮስ በመቅደላ ምሽግ አካባቢ ከፍተኛ የትምህርትና የጸ ሎት ማዕከል የሆነ ቤተክርስቲያን ለመገን ባት ከነበራቸው ሐሳብ ጋር የተያያዘ ነው ። ለቤተመጻሕፍቱ መከፈት ያገለግሉአቸው ዘንድ ለብዙ ዓመታት ልዩ ልዩ የብራናና ባህላዊ መጻሕፍትን አሰባሰቡ ። የተሰበሰ ቡት መጻሕፍትና ሌሎች ጽሑፎችም በአብ ዛኛው የተገኙት ከጐንደር ከተማ ሲሆን በቁጥር 981 የሚሆኑ እንደነበሩ የታሪክ ማሕደሮች ይመሰክራሉ ። ሌሎችም የተሰበ ሰቡ የታሪክ ቅርሶች ነበሩ ። ሪታ ፓንክረ ስት ባቀረቡት ጥናት እንደገለፁት ጽሑፎ ቹንና ቅርሶቹን በሚገባ ለመያዝ በሳምንት አንዴ ወይም ሁለቴ በተፈለገው ሁኔታና መልክ መጠበቃቸውን የሚከታተሉና የሚ ያረጋግጡ ሰዎችም ተመድበው ነበር ።

በ1868 የእንግሊዝ ሠራዊት መቅደላ ላይ ጥቃት ሲሰነዝር ቴዎድሮስ አሰባስበዋ ቸው የነበሩት መጽሐፍት በመቅደላ ከነበ ሩት ከሌሎች የሀገሪቷ ሀብቶች ጋር አብ ረው ተዘረፉ ። ከዝርፊያ በኋላ ምንም ነገር እንዳይቀር በማለት የእንግሊዝ ወታደሮች እነዚህ መጻሕፍትና ውድ ዕቃዎች የነበሩበ ትን ቤት አቃጠሉ ። የተዘረፉት መጻሕፍ ትና ሌሎች ውድ ቅርሶች በ200 በቅሎዎ ችና በ15 ዝሆኖች ተጭነው ከተወሰዱ በኋላ በጨረታ ተሸጠዋል ።

የቴዎድሮስ ሕልፈት

ሪቻርድ ፓንክረስት ባቀረቡት ጥናት እንደገለፁት ቴዎድሮስ "የጊዜያቸውና የሀ

ገራቸው ታላቅ መሪ ነበሩ ። ታላቅ የሚያስ ኛቸው ከነበሩት ታሪካዊ ሕግጋት ጋር የሚጣጣም አስተሳሰብና ተግባር ስለነበራ ቸው ብቻ ሣይሆን ከላይ እንደተዘረዘረው የጊዜያቸውን ችግርና ቅራኔ በመፍታት” ጥንታዊውን የኢትዮጵያ ገናናነት ለማደ ስና ለወደፊቱም ታላቂቱን ኢትዮጵያን ለመገንባት የነበሩትን ዋና ዋና ችግሮች በመረዳት ፣ መፍትሔዎቻቸውንም ለመጠ ቆምና ተግባራዊ እርምጃዎችን ለመውሰድ ላቅ ያለ ተሰጥኦና ችሎታ ስለነበራቸው ነው ።

የቴዎድሮስ ዓላማዎች ከነበሩበት ጊዜ ጋር የሚጣጣም ቢሆንም ከግብ አልደረሰላ ቸውም ። ቴዎድሮስ ሚያዝያ 13 ቀን 1868 ሠራዊታቸውን ይዘው ከእንግሊዝ ወታደ ራዊ የዘመቻ ኃይል ጋር ብዙ ከተዋጉ በኋላ በመጨረሻም የማሸነፍ ተስፋቸው በማከ ተሙ በራሳቸው ሽጉጥ በገዛ እጃቸው ራሳቸ ውን ለሕልፈት አበቁ ። በዚህ ጦርነት የአያሌ ደጋፊዎቻቸውም ሕይወት አል ፏል።

አፄ ቴዎድሮስ ሲሞቱ 50 ዓመታቸው ነበር ። በዚህ ዕድሜያቸው እላይ እንደተጠ ቀሰው በያዙት ዓላማና በጀመሩት ተግባር ቢገፉበት ኖሮ ኢትዮጵያ ዛሬ የምትደርስ በት የዕድገት ደረጃ እጅግ የተሻለ ይሆን እንደነበር መገመት አያዳግትም ።

ቴዎድሮስን ለሕልፈት ያበቃቸው ምን ድነው ? ለቴዎድሮስ ውድቀት ምክንያት ናቸው የሚባሉ የተለያዩ አስተያየቶች ይሰ ነዘራሉ ። አንዳንድ ፀሐፊዎች ለቴዎድሮስ መውደቅ ዋነኛ መንሥኤ አድርገው የሚያ ቀርቡት ግላዊ ባሕርያቸውን ነው ። በመሠ ረቱ ግላዊ ባሕርያቸው አስተዋጽኦ ሊያደ ርግ የሚችል ቢሆንም ዋናው የመውደቃ ቸው መንሥኤ መታየት ያለበት በወቅቱ ከገጠማቸው ውስጣዊና የውጭ ቅራኔ ፣ ከፖለቲካ ኃይል ሚዛን ሁኔታና ግፊት አንፃር ነው ። እነኚህን ቅራኔዎችና የፖለ ቲካ ኃይል አሰላለፍ ሁኔታ ከውጭና ከውስጥ ግንኙነት ማለትም የቴዎድሮስ ዓላማ ተቃዋሚ ከነበሩት ከእንግሊዝ መን ግሥትና ከውስጥ ተፃራሪ ኃይሎች እንቅስ ቃሴ አኳያ ለመመልከት እንሞክር ።

በውጭ ግንኙነት

እንግሊዝ ቀደም ሲል በኦቶማን ቱርክ የበላይነት ተጀምሮ የነበረውን የግብፅን ዓላማ ከራሷ የቅኝ አገዛዝ ፖሊሲ ጋር በማዋሃድ የአባይን ሸለቆና ገባሮቹን ጨምሮ እስከጣና ሐይቅ ድረስ ዘልቆ መያ ዝና ከዚያም ከካይሮ እስከ ኬፐታውን ድረስ ግዛትና መንገድ የመዘርጋት ዓላማ ነበራት ። ይህን ዓላማ ለማሳካት ቆንሲ ሎች፣ የወንጌል ሰባኪዎች ፣ የሃይማኖት መልዕክተኞችና ተመራማሪዎች ናቸው በማለት ሠላዮችን መላክ ጀመረች ። የዚህ ስለላ ሥራ ዓላማ በዘመኑ ተዳክሞ የነበረ ውን የኢትዮጵያን አንድነት በይበልጥ በማ ዳከም ሀገሪቷንና ሕዝቦቿን ለእንግሊዝ ጥገኝነት ወይም ወረራ ማመቻቸት ነበር ። ነገር ግን የአፄ ቴዎድሮስ ጥረት በተቃራኒው ላልቶ የነበረውን የሀገሪቷን አንድነት መልሶ ማጠናከር ነበር ። እነዚህ ተፃራሪ ፍላጐቶች ፣ በቴዎድሮስና በእንግ ሊዝ መንግሥት መሪዎች መካከል አለመጣ ጣምን ፈጠሩ ።

አፄ ቴዎድሮስ ወደ ሀገራቸው የመጡ ትን አውሮፓውያን ለዓላማቸው ማሰለፍ ፈለጉ ። በመጀመሪያ በማግባባትና አንዳን ዴም በማስገደድ ከአውሮፓ ይዘው የመጡ ትን ዕውቀትና ጥበብ በኢትዮጵያ ውስጥ ሥራ ላይ እንዲያውሉ ብዙ ሞከሩ ። ነገር ግን ይህ የቴዎድሮስ ዓላማ ከእንግሊዝ መንግሥት ወኪሎች መሠረታዊ ተልዕኮ ጋር ፍፁም የሚቃረን ስለሆነ (ለሀገራቸው

ጥቅም ሲሉ መጥተው ለኢትዮጵያ ጥቅም መቆም በመሆኑ) ብዙ ጊዜ የሐሳብ ግጭትና አለመግባባት ተፈጠረ ።

በማግባባት አንዳንዴም በማስገደድ አውሮፓውያኑ የአፄ ቴዎድሮስን ዓላማ እስከተወሰነ ደረጃ ድረስ ማገልገል ግድ ቢሆንባቸውም ዋናውን ተልዕኮአቸውን አልዘነጉትም ። በዚህ ምክንያት ነው የቴዎድሮስና የእንግሊዝ ግንኙነት እየተበላሸ የሄደው ። አፄ ቴዎድሮስ በቆንሲል ካሜሮን አማካይነት በ1862 ለንግሥት ቪክቶሪያ ደብዳቤ ፃፉ ። ይህ ደብዳቤ ቱርኮችና ግብፆች በምፅዋ በኩል ወደ ኢትዮጵያ እየገቡ የኢትዮጵያን ዳር ድንበር መድፈራቸውን በመግለፅ በዲፕሎማቲክ ደረጃ የጠበቀ ወዳጅነትና ዕርዳታ እንዲደረግላቸው የሚጠይቅ ነው ። ሆኖም ቴዎድሮስ ለዚህ ደብዳቤያቸው መልስ ሳያገኙ ሁለት ዓመታት አለፉ ።

ደብዳቤያቸው ምላሽ ከማጣቱም በተጨማሪ ካሜሮን ከቴዎድሮስ ደብዳቤ ተቀብሎ በታዘዘው መሠረት ከመፈፀም ይልቅ በወቅቱ ከኢትዮጵያ ጋር ጠላት ወደሆነችው ጐረቤት አገር ግብፅ ድርሶ እንዲመለስ በእንግሊዝ መንግሥት ታዘዘ ። ይህም ትዕዛዝ እንግሊዞች በሰሜን ምሥራቅ አፍሪቃ የተስፋፊነት ፖሊሲዎች የሚያራምዱትን ቱርክንና ግብፅን ይረዳሉ በማለት ቴዎድሮስ ቀደም ሲል ያደረባቸውን ጥርጣሬ ይበልጥ ግልፅ እያደረገላቸው መጣ ። ለደብዳቤዎቻቸው መልስ በማጣታቸውና አለመግባባት በመፈጠሩ ቴዎድሮስ ካሠራቸው ሚሲዮናውያን በተጨማሪ ቆንሲል ካሜሮንና ጸሐፊውን ፡ ትንሽ ቆይተውም ግብፃዊውን አቡነ ሰላማን አሠሩ ።

በጊዜው አፄ ቴዎድሮስ ይህንን የእሥራት እርምጃ በአውሮፓውያን ላይ የወሰዱበትን ምክንያት ለጃን የተባለው በምፅዋ የፈረንሳይ ቆንሲል ላቀረበላቸው ጥያቄ ሲመልሱ "የአውሮፓን መንግሥት ዘዴ እኔ አውቃለሁ ፤ በእንደኛ ያሉ ሀገሮች ላይ ሥልጣን ለመዘርጋት ሲፈልጉ በመጀመሪያ ሚሲዮናውያኖችን ወይንም ወንጌል ሰባኪዎችን ይልካሉ ፤ ከዚያም ወንጌል ሰባኪዎችን የሚረዳ ቆንሲል ይልካሉ ፤ ከዚያም ቆንሲል የሚረዳ ጦር ይልካሉ ።" ብለዋል ።

የአውሮፓውያኑ መታሰር በእንግሊዝ ውስጥ እንደተሰማ ለደብዳቤያቸው መልስ ሳይሰጣቸው የቆዩት ቴዎድሮስ በእንግሊዝ ንግሥት ፊርማ መልስ አገኙ ። ቴዎድሮስ ቀደም ሲል እንዲላኩላቸው ጠይቀዋቸው የነበሩት የዕደ ጥበባት ባለሙያዎችም በምፅዋ በኩል ተላኩ ። ይህ ለጊዜው ለቴዎድሮስ እርካታ በማስገኘቱ እሥረኞች ተለቀቁ።

ነገር ግን በመጀመሪያ ደረጃ እሥረኞች ካልተፈቱና ምፅዋ ድረስ ካልተላኩ መልስ የተሰጠባቸው ነገሮች ሁሉ ተግባራዊ እንደማይሆኑ ከንግሥት ቪክቶሪያ የተላከው ደብዳቤ ያመለክት ነበር ። አፄ ቴዎድሮስም የምፅዋ አካባቢ በወቅቱ በቱርክና በግብፅ ቁጥጥር ሥር በመሆኑ እስረኞቹን በዚያ በኩል ለመላክ አልፈለጉም ነበር ። ስለዚህ ቴዎድሮስ "በምፅዋ አካባቢ ችግር ስላለ በመተማ በኩል እሥረኞችን ፈትቼ እልካለሁና ሙያተኞችም በዚያው በኩል እንዲመጡ ይደረግልኝ" በማለት ለእንግሊዝ መንግሥት ጥያቄ አቀረቡ ። ይህ የአፄ ቴዎድሮስ ጥያቄ ለእንግሊዞች ዘንድ ተቀባይነት ባለማግኘቱ "ሙያተኞቹ" ወደሀገራቸው እንዲመለሱ ተደረገ ። ይህ ድርጊት ያበሳጫቸው አፄ ቴዎድሮስ የእንግሊዝን ደብዳቤ ይዞ የመጣውን ራሳምን ጨምረው አውሮፓውያንን እንደገና አሠሩ ። ይህም እርምጃ በአፄ ቴዎድሮስና በእንግሊዝ መንግሥት መሪዎች መካከል የነበረው ግንኙነት ከዕለት ወደ ዕለት የጠላትነት አዝማ

ሚያ እየያዘ መሄዱን በጉልህ አሳየ ። ወደፊት እንደምናየው ግንኙነቱ የበለጠ በመሻከሩ የእንግሊዝ መንግሥት መሪዎች የታሠሩትን መልዕክተኞቻቸውንና ዜጎቻቸውን ለማስፈታት በሚል ሰበብ የጦር ኃይል ላኩ ።

የውስጥ ሁኔታ ፡

ለቴዎድሮስና ለዓላማቸው መቀጨት ዋናው መንሥኤ በሀገር ውስጥ የነበረው ቅራኔ ነው። ቅራኔው የተከሰተው በቴዎድሮስና ደጋፊዎቻቸው በነበሩት የኅብረተሰብ ክፍሎች ማለትም ለተራማጅ አስተሳሰብ ፣ አሠራርና ዓላማ የቆሙት በአንድ በኩል የማዕከላዊ መንግሥትን ግዛቶች ተጠናክሮ መመሥረትና የቴዎድሮስን የማኅበራዊ ለውጥ ውጥኖች የማይደግፉ ኃይሎች በሌላ በኩል ሆነው የሚያካሂዱት ትግል ነበር ። አፄ ቴዎድሮስ ዓላማቸውን ተግባራዊ ለማድረግ ሀገሪቷን በብዙ ቦታ በመቀራመት ይገዙ የነበሩትን መሳፍንትና መኳንንት መታገል ነበረባቸው ። በመሆኑም በመቅደላ ጦርነት ዋዜማ ቀደም ሲል ንጉሡ በአካባቢ መሳፍንትና ባላባቶች ላይ በወሰዱአቸው ልዩ ልዩ እርምጃዎች ፣ በጀመሩት ማኅበራዊ ለውጥ ፣ ረጅም ጊዜ የኖረውን ወግ አጥባቂ አስተሳሰብና ልምድ በመፃረራቸው ምክንያት ከፍተኛ የፖለቲካ ችግር ገጥሟቸው ነበር ። ይህም ሁኔታ አፄ ቴዎድሮስን ለውጭ ኃይል ጥቃት ሊያጋልጣቸው ችሏል ።

ተቀናቃኞቻቸው አፄ ቴዎድሮስን ማኅበራዊ መሠረት ለማሳጣት ፣ በሕዝቡ ዘንድ ተወዳጅነትና ተቀባይነት እንዳይኖራቸው ለማድረግ ሲሉ ከፍተኛ የሆነ የሥነ ልቡና ዘመቻ ያደርጉባቸው ነበር ። ለዚህም የአፄ ቴዎድሮስ የትውልድ ምንጭ በተለይ በእናታቸው በኩል የንጉሥ ቤተሰብ አለመሆን ከፍተኛ መሣሪያ በመሆን አገልግሏል ።

የታሪክ ምሁር የሆኑት ዶክተር ታደሰ ታምራት እንዳሉት በፊውዳላዊ አስተሳሰብ መሠረት ቴዎድሮስ በአባታቸው በደጃዝማች ኃይሉ ወ/ጊዮርጊስ ከጨዋ (ከፊውዳሉ) ቤተሰብ መሆናቸው በጥቅሉ ተቀባይነት ነበረው ። እናታቸው ወይዘሮ አትጠገብ ግን ለፊውዳላዊው አሉባልታና ሽኩቻ ክፉኛ ተጋልጠው ነበር ። የቴዎድሮስ ጠላቶች እኚህ ሴት ኮሶ ሻጭ ነበሩ በማለት ያጥላላሉ ። የዚህም ማጥላላት ዓላማ ቴዎድሮስ “የመንግሥት ሥልጣን መያዝ አይገባቸውም ፤ የደሃ ልጅ ናቸው ፤ የንጋሢነት ዘር የላቸውም ፤ ሀገርን ፣ ሕዝብን መምራት ከሚችል ቤተሰብ አልተወለዱም” የሚል ፊውዳላዊ እምነት በሕዝቡ ዘንድ ማስፋፋት ነበረ ።

በእርግጥ ቴዎድሮስ የነገሡት በብቃታቸው እንጂ ከነጋሢው ዘር በውርስ የተላለፈላቸውን ዘውድ ወርሰው አልነበረም ። ይህ በመሆኑ ደግሞ ንጉሥ መሆን አይገባቸውም ነበር ከሚል መደምደሚያ አያደርስም ። በማኅበራዊ መስክ ሰው ከሰው ልቆ የሚገኘው የዘመኑ ተጨባጭ ሁኔታ በፈጠረለት ማኅበራዊ ሥፍራ እንጂ በደምና በአጥንት አይደለም ። በሥነ ሕይወት እንፃርም ቢሆን ለገዥነትና ለተገዢነት ተለይቶ የተፈጠረ ዘርም የለም ። ነገር ግን ፊውዳሎች ሥልጣን ከእጃቸው እንዳይወጣ ሲሉ የሌላቸውን ኃይልና ጥራት አለን እያሉ በአስፋፉት አስተሳሰብና በፈጠሩት የፖለቲካ ሥርዓት ሥልጣን ከአንዱ ግለሰብ ወደ ሌላው ሲሸጋገር ቆይቷል ። ቴዎድሮስ ከዚህ ዓይነቱ ሰንሰለት ውጭ በብቃታቸው የነገሡ ናቸው ።

ከላይ በተጠቀሰው መልክ መንገሣቸው ብቻ ሣይሆን ከነገሡ በኋላ የወሰዱአቸውን ዕርምጃዎች ማለትም የአካባቢ መሳፍንት

ንና ባላባቶችን የፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ ማስወገዳቸው ወይም ለማስወገድ መጣራቸው፣ ሽፍቶችን በመቆጣጠር ሰላም ማስፈናቸው፣ የመሬት ይዞታ ለውጥ ለማድረግ መሞከራቸው ፣ በየጊዜው በተፈታተኗቸው ኃይሎች ላይ ጥብቅ እርምጃ መውሰዳቸውና የሚያፈልቁአቸው አዳዲስ ሐሳቦች፣ አሠራሮችና ሥልቶች ከውስጥና ከውጭ የነበሩትን ቅራኔዎች አወሳሰቡባቸው ። ኤድዋርድ ኡልዶርፍ የሚባሉት ታሪክ ጸሐፊ እንዳሉት የቴዎድሮስ ለውጥ ብዙኃኑ ሕዝብ በደስታ የተቀበለው ቢሆንም በፊውዳሎች ዘንድ ተቃውሞን አስከተለ ።

የቴዎድሮስ ለውጥ ፈላጊነትና አራማጅነት ፣ አንዲት ጠንካራና ዝነኛ የሆነች ኢትዮጵያ የመመሥረት ፍላጐት በውስጥና በውጭ ጠላቶቻቸው ዘንድ በበጐ ባለመታየቱ ፀረ ቴዎድሮስ ግንባር እንዲፈጥሩ አድርጓቸዋል ። የውጭ መንግሥታት ወኪሎች መሠሪ ተልዕኮአቸውን ለማሳካት እንቅፋት የሆኑባቸው ቴዎድሮስ እንዲወገዱላቸው ወይም እነሱ እንደፈለጉት እንዲሆኑላቸው ፤ የውስጥ ተቀናቃኞቻቸውም ለየግል ጠባብ ፍላጐታቸው መሳካት ሲሉ ለቴዎድሮስ መውደቅ ታግለዋል ።

በዚህም ምክንያት ደራሲ ማሞ ውድነህ ባቀረቡት ጥናታዊ ጽሑፍ እንደገለጹት “ለአሥራ ሁለት ዓመታት ያህል በድል አድራጊነት ፣ በተስፋ ፣ በሰላም በአስፈሪነትና በዝነኛነት” የቆየው የቴዎድሮስ ዘመነ መንግሥት በመጨረሻዎቹ “ሁለት ዓመታት በብርቱ ፈተና ፣ በሀዘን ፣ በብስጭት ፣ በቁጣና በብቀላ” በከረረና በመረረ ቅራኔ መጓዝ ግድ ሆነበት ፣ ከውስጥ በነበሩት ቅራኔዎች ምክንያት ቴዎድሮስ ለጥቃት መመቻቸታቸውን የተረዳው የእንግሊዝ መንግሥት 32,000 ወታደሮችን የያዘና በሮበርት ናፒየር የሚመራ የእንግሊዝ ወታደራዊ የዘመቻ ኃይል የታሠሩ የእንግሊዝ ዜጎችን ለማስፈታት በሚል ሽፋን ከቦምቤ (ሕንድ) በመነሣት ወደ መቅደላ ጉዞ ቀጠለ ። ወራሪው ሠራዊት መቅደላ እስኪደርስ ድረስ ጉዞው የተመቻቸለት በአካባቢ ባላባቶች ድጋፍ ወይም ገለልተኝነት ነበር ። በተጨማሪም ለተልዕኮውም መሳካት አስፈላጊውን ዝርዝር መረጃ ያገኘውም ከእነኚሁ ከቴዎድሮስ ተቃዋሚዎች ነበር ።

ወራሪው ሠራዊት መቅደላ እንደተቃረበ ጦርነት ተከፈተ ። አፄ ቴዎድሮስ ለዘመናዊ መሣሪያ እጅግ ይጓጉ የነበረው ይህን ዓይነት ጥቃት ለመከላከል ነበር ። ሆኖም ዓላማቸው ባለመሳካቱ በቂ የጦር መሣሪያ አልነበራቸውም ። ዶክተር ግርማ ኪዳኔ ባቀረቡት ጥናታዊ ጽሑፍ እንደገለጹት ቴዎድሮስ በጋፋት ላይ ባሠሩአቸው ትናንሽና ትላልቅ መድፎች ፣ ከውጭ በስጦታ በተሠጣቸውና በገዟቸው ጥቂት መሣሪያዎች ፣ እንዲሁም በጦርና በጐራዴ ተዋጉ ። ወራሪው ሠራዊት ግን በጣም ዘመናዊ የሆኑ የጦር መሣሪያና ሮኬት በመጠቀም ማጥቃቱን ቀጠለ ። ቴዎድሮስም በጠላት እጅ ከመማረክ የእራሳቸውን ሕይወት በእጃቸው አሳለፉ ።

የእንግሊዝ ሠራዊት ንጉሡ ከሞቱ በኋላ በቡድን እየተከፋፈለ ለዘረፋ በመሰማራት ከብርና ከወርቅ የተሠሩ ጐራዴዎችንና ጋሻዎችን ፣ አንድ ሺህ አካባቢ የሚደርሱ የብራና መጽሐፎችን (ንጉሡ ለማቋቋም ላቀዱት ቤተመጻሕፍት የሰበሰቧቸው ናቸው ።) የተለያዩ ቅርፅና ይዘት ያላቸው የወርቅ ፣ የብርና የመዳብ መስቀሎችን ፣ ከአንበሳ ቆዳ የተሠራ ለምድ ፣ ልዩ ልዩ ቀለማት ያላቸው ድንኳኖችና ሌሎች ልዩ ልዩ የቤት ቁሳቁሶችን ፣ የንጉሠ—ነገሥቱን ማኅተም ፣ አራት የሚሆኑ ዘውዶች ፣ ከንፁህ ወርቅ የተሠራ የአቡኑን አክሊል ፣ ከንፁህ ወርቅ የተሠራ ጽዋ ፣

ደብዳቤዎችንና ሠነዶችን ፣ በዛ ያሉ ጋሻዎችን ፣ ሌሎችም ምርጥ የሆኑ ቅርሶችን ዘረፈ።

ወታደሮቹ በየግላቸው መርጠው የያዟቸው ውድ ዋጋ ያላቸው ዕቃዎች ቀርተው ሌሎች በጨረታ እንዲሸጡ ተወሰነ ። የጨረታው ዓላማ ባንድ በኩል ከጨረታው የሚገኘውን ገንዘብ በጦርነቱ ለተሳተፉት ወታደሮች ለማካፈል ሲሆን በሌላ በኩል ለብሪትሽ ሙዝዬም ሰፊ ዕድል ለመስጠት ነው ።

የእንግሊዝ መንግሥት ቢያመቸው ሠራዊቱን አዝምቶ በፈጸመው ጥቃትና ዘረፋ ብቻ ባላበቃ ነበር ። የዘመኑ ቀንደኛ ቅኝ ገዢ ኃይል እንደመሆኑ በኢትዮጵያም ላይ ተጽዕኖውን ባሳረፈ ነበር ፤ ነገር ግን ይህ ሊሆን አልቻለም ፤ ዋንኛው ምክንያትም የኢትዮጵያ ሕዝብ በረጂም ታሪኩ እንዳስመሰከረው ለነፃነቱ ብርቱ ተጋዳይ መሆኑ ነው ። ስለዚህ የእንግሊዝ ወራሪ ሠራዊት በግንቦት ወር 1868 ለቅቆ ለመውጣት ተገደደ።

ማጠቃለያ

የቴዎድሮስ ዘመነ መንግሥት አሥራ አራት ዓመታት የኢትዮጵያን ታሪክ ከአንድ አቅጣጫ ወደሌላ አቅጣጫ መልሰውታል። ማዕከላዊ መንግሥት የተዳከመበትና ሀገሪቷ ለውጭ ወራሪ የተጋለጠችበት ዘመን እንዲያከትምና አንድነቱ የፀና ፣ ነፃነቱ የተረጋገጠ ፣ዳር ድንበሩ የታፈረ ፣ በእምነቱና በዕድገቱ የላቀ መንግሥት እንደገና እንዲመሠረት ጽኑ መሠረቶች ተተክለዋል ።

አፄ ቴዎድሮስ ለሀገራቸው አንድነት ፣ ለሕዝባቸው ነፃነትና ክብር ሲታገሉ አልፈዋል ፤ የዛሬው ትውልድ ከእርሳቸው ተጋድሎ የሚማረው እጅግ ብዙ ነው ። ታሪክን የምናጠናው ለዕውቀትነቱ ፣ የታሪክ ሰዎችን ፣ ቦታዎችንና ሀገሮችን ለመገንዘብ ስንል ብቻ አይደለም ። ዛሬ የተደረሰበትን የዕድገት ደረጃ በትክክል ለመረዳት ፣ የወደፊቱን በትክክል ለመቀየስ ነው ። በመሆኑም አፄ ቴዎድሮስን ለጥቃት ስላመቻቿቸው ሁኔታዎች ስናወሳ ዛሬም ለሕዝባዊ ዓላማችን ዳር መድረስ እንቅፋት የሚሆኑ ችግሮችን በትክክል በማጤን ለማስወገድ ተገቢ ጥረት ማድረግ እንዳለብን መገንዘብ ይኖርብናል ። ዛሬም የአብዮታችንን ግኝቶች ከንቱ ለማስቀረትና አልፎ ተርፎም የአገራችንን አንድነት ለማፍረስ የውስጥና የውጭ አድኅሮት የሚያደርጉትን ሙከራ ለመቅጨትና የታፈረች ሕዝባዊት ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን ለመገንባት ሐቀኛ ዜጋ ሁሉ ኅብረቱን አጠናክሮ መታገል ይጠበቅበታል ።

Proudly brought to you by

www.binyamhk.wordpress.com

ዋጋው ብር 1.25

B.S.P.P